chilot.wordpress.com

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 44
ADDIS ABABA 28th July 2010

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፹፯/፪ሺ፪
የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.... ገፅ ፭ሺ፫፻፹፫

CONTENTS

Regulation No. 187/2010
Defense Construction Design Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation ………….Page 5383

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፯/፪ሺ፪

## የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ «የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፯/፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>መቋቋም</u>

፩) የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪) ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩) በዋነኛነት የሀገሪቱን የመከላከያ ግንባታ ፍላጎት ለማሟላት ማንኛውንም የዲዛይን እና ኮንትራት አስተዳደር ሥራዎችን መሥራት፤

## Council Of Ministers Regulation No. 187/2010

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF DEFENSE CONSTRUCTION DESIGN ENTERPRISE.

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. ***<u>Short Title</u>***

This Regulation may be cited as the "Defense Construction Design Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 187/2010".

2. ***<u>Establishment</u>***

1) The Defense Construction Design Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. ***<u>Supervising Authority</u>***

The Ministry of National Defense shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. ***<u>Head Office</u>***

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. ***<u>Purposes</u>***

The purpose for which the Enterprise is established are:

1) to engage in design and contract administration activity mainly to satisfy the national defense construction needs;

chilot.wordpress.com



፪) በተጓዳኝ የመንገድ፣ የግድብ፣ የመስኖ፣ የሕንፃና ሌሎች የማማከር፣ የዲዛይንና የኮንትራት አስተዳደር ሥራዎች መሥራት፤

፫) ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን መሥራት።

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፴ ሚሊዮን (ሰላሳ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፩ ሚሊዮን ፭፻፸፭ሺ (አሥራ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2) in parallel, to engage in the construction of roads, dams, irrigation infrastructures, buildings and other consulting, design and contract administration works;

3) to engage in any other related activities necessary to the attainment of its purposes.

6. ***Capital***

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 30,000,000.00 (Thirty Million Birr) of which Birr 11,575,000.00 (Eleven Million Five Hundred Seventy Five Thousand) is paid up in cash and in kind

7. ***Liability***

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. ***Duration***

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. ***Effective Date***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of July, 2010.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA